**ጉትማከር-ላንሴት ኮሚሽን**
ስለወሲባዊና ስነተዋልዶ ጤና እና መብቶች

**አኅጽሮተ ሪፖርት**

# ዕድገትን ማፋጠን

## የወሲባዊና ስነተዋልዶ ጤና እና መብቶች ለሁሉም

## ኮሚሽኑ

የጉትማከር-ላንሴት ኮሚሽን ሪፖርት ያልተጠናቀቀውን የወሲባዊና ስነተዋልዶ ጤና እና መብቶች (SRHR) አጀንዳ መጠነ ርዕይ ያሳያል፤ በሰብአዊ መብቶች ውስጥ ሥር ለያዘው የወሲባዊና የስነተዋልዶ ጤና እና መብቶች ጉዳይ ደፈር ያለ እና በማስረጃ ላይ የተመሠረተ ራዕይ አጥርቶ ያወጣል፤ ይህንን ራዕይ ለመምራትም ለወሲባዊና ስነተዋልዶ ጤና እና መብቶች የተቀናጀ አዲስ ብያኔ ይሰጣል፤ እንዲሁም በወል ከሚታወቁት የወሲባዊና የስነተዋልዶ ጤና ማዋቀሪያዎች አልፎ የተሟላ የመሠረታዊ የወሲባዊና ስነተዋልዶ ጤና እና መብቶች ሥራዎችን ጥቅል በምክረ ሐሳብነት ያቀርባል። ሪፖርቱ በወሲባዊና ስነተዋልዶ ጤና እና መብቶች ላይ ኢንቨስት ማድረግ ከጤና ብቻ ሳይሆን ከሰፊው ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ልማት አንጻር ስለሚኖረው ጠቀሜታም ያስገነዝባል።

ኮሚሽኑ ከአፍሪካ፣ ከእስያ፣ ከአውሮፓ፣ ከመካከለኛው ምሥራቅ፣ ከሰሜን እና ደቡብ አሜሪካ በተውጣጡ፣ በተለያዩ ሙያዎች በተካኑ እና በሰፊውም በወሲባዊና ስነተዋልዶ ጤና እና መብቶች ጉዳዮች ላይ የመሥራት ልምድ ባካበቱ 16 ኮሚሽነሮች የተዋቀረ ነው። ኮሚሽኑ ከ2016 እስከ 2018 በርካታ ምክክሮችን አድርጓል፤ በጉትማከር ኢንስቲቲዩት፣ በአፍሪካን ፖፑሌሽን ኤንድ ኸልዝ ሪሰርች ሴንተር እና ከብዙዎቹ ኮሚሽነሮች ጋር ተዛማጅነት ባላቸው ሌሎች ድርጅቶች ተመራማሪዎች ድጋፍ ያለውን ማስረጃም አቀናጅቷል። የኮሚሽኑ የአማካሪ ቡድን ከወሲባዊና የስነተዋልዶ ጤና እና መብቶች፣ ከዓለማቀፍ ጤና፣ እና በሪፖርቱ እና በምክረ ሐሳቦቹ ላይ ጠቃሚ ግብረ መልስ ከሰጡ ፈንድ አድራጊ ድርጅቶች የተወከሉ 23 አባላትን ይዟል።

## ኮሚሽነሮች

**አን ኤም ስታርስ**
ጉትማከር ኢንስቲቲዩት• ኒው ዮርክ፣ ኤንዋይ፣ ዩኤስኤ

**አሌክስ ሲ ኤዜህ**
ዩኒቨርሲቲ ኦፍ ዘ ዊትዋተርስራንድ • ጆሐንስበርግ፣ ደቡብ አፍሪካ

**ጋሪ ባርከር**
ፕሮሙንዶ • ዋሺንግተን፣ ዲሲ፣ ዩኤስኤ

**አላካ ባሱ**
ኮርኔል ዩኒቨርሲቲ • ኢታካ፣ ኤንዋይ፣ ዩኤስኤ

**ጄን ቲ በርትራንድ**
ቱላኔ ዩኒቨርሲቲ • ኒው ኦርሊየንስ፣ ኤልኤ፣ ዩኤስኤ

**ሮበርት ብሉም**
ጆንስ ሆፕኪንስ ዩኒቨርሲቲ • ባልቲሞር፣ ኤምዲ፣ ዩኤስኤ

**አዋ ኤም ኮል-ሴክ**
የሴኔጋል መንግሥት • ዳካር፣ ሴኔጋል

**አናንድ ግሮቨር**
ሎየርስ ኮሌክቲቭ • ዴልሂ፣ ህንድ

**ላውራ ላስኪ**
ኧርሊ ሲግናል ፋውንዴሽን • ኒው ዮርክ፣ ኤንዋይ፣ ዩኤስኤ

**ሞኒካ ሮአ**
የግል ኮንሰልታንት

**ዜባ ኤ ሳታር**
ፖፑሌሽን ካውንስል • ኢዝላማባድ፣ ፓኪስታን

**ላሌ ሴይ**
የዓለም ጤና ድርጅት • ጄኔቫ፣ ስዊዘርላንድ

**ጋማል አይ ስሩር**
አል አዝሃር ዩኒቨርሲቲ • ካይሮ፣ ግብፅ

**ሱሺላ ሲንግ**
ጉትማከር ኢንስቲቲዩት• ኒው ዮርክ፣ ኤንዋይ፣ ዩኤስኤ

**ካሪን ስቴንበርግ**
የዓለም ጤና ድርጅት • ጄኔቫ፣ ስዊዘርላንድ

**ማርሊን ቴመርማን**
አጋ ኻንዩኒቨርሲቲ • ናይሮቢ፣ ኬኒያ

በወሲባዊና በስነተዋልዶ ጤና እና መብቶች ውስጥ ያሉ ክፍተቶች በመላው ዓለም ባሉ ግለሰቦች፣ ማኅበረሰቦች እና ኢኮኖሚዎች ላይ ትልቅ ጥፋት እያስከተሉ ነው። እነዚህን ክፍተቶች መድፈን ሁሉም ሰዎች በአካሎቻቸው ላይ - ከመገለል፣ ከመድልዎ፣ ከግዳጅ ነጻ ሆነው - የመወሰን እና መሠረታዊ የወሲባዊና የተዋልዶ ጤና አገልግሎቶች የማግኘት መብቶቻቸውን የሚያጠቃልል ሁሉን አካታች ዘዴ ይጠይቃል። የጉትማከር -ላንሴት ኮሚሽን የወሲባዊና ስነተዋልዶ ጤና እና መብቶች ሁለንታዊ ተደራሽነት ራዕይ ወጪው ተመጣጣኝ፣ ሊደረስበት የሚችል እና የጤና፣ የፍትሐዊ ልማት እና ሰብአዊ መብቶችን ለሁሉም ሰው ለማሳካትም ወሳኝነት ያለው ነው።

ወሲባዊና የስነተዋልዶ ጤና እና መብቶች ለሰዎች ጤንነት እና ሕልውና፣ ለሥርዓተ ጾታ እኩልነት እና ለሰው ልጅ ደህንነት ወሳኝ ናቸው። የብዙ አስርት ዓመታት ጥናት ያሳየው - አሁንም የሚያሳየው - በወሲባዊ እና የስነተዋልዶ ጤና ላይ ኢንቨስት ማድረግ ጥልቅ እና ሊሰፈሩ ሊቆጠሩ የሚችሉ ጠቀሜታዎች እንዳሉት ነው። ስለዚህም፣ መንግሥታት በአያሌ ዓለማቀፍ ስምምነቶች አማካይነት፣ በዚህ ኢንቨስትመንት ላይ በቁርጠኝነት እየሠሩ ነው። ሆኖም፣ ደካማ የፖለቲካ ቁርጠኝነት፣ በቂ ሀብት ማጣት፣ በሴቶች እና በልጃገረዶች ላይ የሚደረግ ጽኑ መድልዎ፣ እንዲሁም ከወሲባዊነት ጋር የተዛመዱ ጉዳዮችን በግልጽ እና በምልዓት ለማስተናገድ ፈቃደኛ አለመሆን ዕድገቱን በተደጋጋሚ ገትተውታል።

**በታዳጊ አገሮች በየዓመቱ፡-**

- ከ200 ሚሊዮን በላይ ሴቶች ያልተፈለገ እርግዝናን ማስቀረት ቢፈልጉም፣ ዘመናዊ የወሊድ መቆጣጠሪያ ዘዴዎችን እየተጠቀሙ አይደሉም
- ከ45 ሚሊዮን በላይ ሴቶች በቂ ወይም ምንም የቅድመ ወሊድ እንክብካቤ አያገኙም
- ከ30 ሚሊዮን በላይ ሴቶች ልጆቻቸውን በጤና ተቋማት አይወልዱም

**በመላው ዓለም፣ በየዓመቱ፡-**


- 25 ሚሊዮን አደገኛ የጽንስ ማቋረጦች ይደረጋሉ
- ከ350 ሚሊዮን በላይ ሴቶች እና ወንዶች ከአራቱ መዳን የሚችሉ የአባላዘር በሽታዎች ለአንዱ ህክምና ያስፈልጋቸዋል
- ወደ ሁለት ሚሊዮን የሚጠጉ አዳዲስ የኤችአይቪ መያዞች ይመዘገባሉ
- በግምት 266,000 ሴቶች በማህፀን ጫፍ ካንሰር ይሞታሉ

እንዲሁም በመላው ዓለም፣ በሕይወታቸው የሆነ አጋጣሚ ላይ ከሦስት ሴቶች አንዷ በቅርብ አጋር ጥቃት ወይም አጋር ባልሆነ ሰው በሚሰነዘር ጥቃት መልክ በጾታ ላይ የተመሠረተ ጥቃት ይደርስባታል።

በመጨረሻም፣ ሁሉም በተዋልዶ ዕድሜ ላይ ያሉ ሰዎች - 4.3 ቢሊዮን ሰዎች - በዚህ የተዋልዶ ዕድሜያቸው ውስጥ ከመሠረታዊ የወሲባዊና የስነተዋልዶ ጤና አገልግሎቶች ቢያንስ አንዱን ያጣሉ።

ዓለማቀፉ ማኅበረሰብ ይህንን ክፍተት ችላ ብሎም ይሁን ታግሶ መቀጠል አይችልም - መቀጠልም የለብንም። ፈጣኑ የቴክኖሎጂ ለውጥ እርምጃ፤ የባለፉት 20 ዓመታት የጤና፣ የትምህርት እና የኢኮኖሚ ትሩፋቶች የተገኘው ኃይል፤ እንዲሁም በጉጉት የተሞሉት አዲሶቹ የልማት ግቦች በወሲባዊ እና የስነተዋልዶ ጤና እና መብቶች - ይኸውም በጤና እና ሰብአዊ መብቶች - ላይ ዕድገት የማስመዝገቡን ጉዳይ የሚቻል ያደርጉታል።

በዓለማቀፍ ደረጃ ወሲባዊና የስነተዋልዶ ጤና እና መብቶችን ማሳካት የሚያስችሉ መንገዶች እና እውቀቶች አሉን። ወሲባዊና የስነተዋልዶ ጤና እና መብቶችን በሰዎች ሕይወት ውስጥ እውን ማድረጊያው ጊዜ አሁን ነው።




# አዲስ ብያኔ

**በታህሳስ 1994 ከተደረገው የስነሕዝብ እና ልማት ዓለማቀፍ ጉባዔ ወዲህ፣** ዓለማቀፍ የጤና እና የሰብአዊ መብቶች ማኅበረሰቦች በዚህ ጊዜ ውስጥ መሻሻሎችንም እንቅፋቶችንም እያዩ ወሲባዊና የስነተዋልዶ ጤና እና መብቶችን ለመበየን እና ለማሻሻል ሲሠሩ ቆይተዋል። ምንም እንኳን የወሲባዊና የስነተዋልዶ ጤና እና መብቶች ማኅበረሰቡ እያንዳንዱ የወሲባዊና የስነተዋልዶ ጤና እና መብቶች ጉዳይ ከሌሎቹ ጉዳዮች ጋር የተሳሰረ መሆኑን፣ ብሎም ወሲባዊና የስነተዋልዶ መብቶችን ማሳካት ወሲባዊ እና የስነተዋልዶ ጤናን ለማሳካት ወሳኝ መሆኑን በስፋት ቢገነዘብም፣ አብዛኞቹ ዓለማቀፍ ስምምነቶች ግን ስለወሲባዊና የስነተዋልዶ ጤና እና መብቶች ጠባብ አተያይ ነው ያላቸው።

ኮሚሽኑ መንግሥታት፣ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅቶች፣ ሲቪል ማኅበረሰቡ እና ሌሎች ቁልፍ ባለድርሻ አካላት በዓለማቀፍ ውይይቶች እምብዛም የማይነሱትን እንደ ወሲባዊ ደህንነት እና ግላዊ ነጻነት ያሉ የሁሉንም ሰዎች ፍላጎቶች እና አገልግሎቶች ላቀናጀ አዲስና ሁሉን አቀፍ የወሲባዊና የስነተዋልዶ ጤና እና መብቶች ብያኔ እንዲሠሩ ጥሪውን ያቀርባል። በበርካታ ዓለማቀፍ እና ክፍለ ዓለማዊ ስምምነቶች እንዲሁም በዓለማቀፍ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች እና መርሆች ላይ የተገነባው አዲሱ ብያኔ የሁሉንም ግለሰቦች ወሲባዊና የስነተዋልዶ ጤና ፍላጎቶች ለመድረስ በሚያስችሉ አገልግሎቶች እና እርምጃዎች ላይ እያቆጠቆጠ ያለ የጋራ ስምምነት መኖሩን ያንፀባርቃል። ይሄ ብያኔ ባለድርሻ አካላት ሁሉንም የወሲባዊና የስነተዋልዶ ጤና እና መብቶች ጉዳዮች የሚያዳርሱ ፖሊሲዎችን፣ አገልግሎቶችን እና ፕሮግራሞችን የሚቀርፁበት ሁለንታዊ ማዕቀፍ ይሰጣል።

## *የወሲባዊና የስነተዋልዶ ጤና እና መብቶች የተቀናጀ ብያኔ*

**ወሲባዊና የስነተዋልዶ ጤና ከሁሉም ጾታዊ እና የስነተዋልዶ ጉዳዮች ጋር የተያያዘ የአካል፣ የስሜት፣ የአእምሮ እና ማኅበራዊ ደህንነት ነው፤ ይህ የበሽታ፣ የአካላዊ/ አእምሯዊ አሠራር መስተጓጎል ወይም የአቅመ ቢስነት አለመኖር ማለት ብቻ አይደለም። ስለዚህም አወንታዊ የወሲባዊና የስነተዋልዶ ዘዴ ራስ ከበሬታን እና ጠቅላላውን ደህንነት ለማሳደግ አስደሳች ወሲባዊ ጉድኝቶች፣ መተማመን እና ተግባቦት ለሚጫወቱት ሚና ዕውቅና መስጠት ይኖርበታል። ሁሉም ግለሰቦች የአካሎቻቸውን አያያዝ በተመለከተ የመወሰን እና ይህንንም የሚደግፉ አገልግሎቶችን የማግኘት መብቶች አሏቸው።**

የወሲባዊና የስነተዋልዶ *ጤናን* ማሳካት፣ የወሲባዊ እና የስነተዋልዶ *መብቶች* መከበር ላይ ይወሰናል፤ መብቶቹም የሚመሠረቱት ሁሉም ግለሰቦች ባሏቸው፡-

- አካላዊ ክብራቸውን፣ ምስጢራቸውን እና በራስ የማዘዝ ግላዊ መብታቸውን የማስጠበቅ፣
- የወሲባዊ ሁኔታ ምርጫቸውን እና የስርዓተ ጾታ ማንነታቸውን እና መግለጫቸውን ጨምሮ የገዛ ወሲባዊ ሁኔታቸውን በነፃነት የመበየን፣
- ወሲባዊ ግንኙነት መጀመር ይኑርባቸው አይኑርባቸው እና መቼ የሚለውን የመወሰን፣
- የወሲብ ተጣማሪዎቻቸውን የመምረጥ፣
- ደህንነታቸው የተጠበቀ እና አስደሳች ወሲባዊ ተመክሮዎችን የማጣጣም፣
- ማግባት ይኑርባቸው አይኑርባቸው፣ እና መቼ እና ማንን እንደሚያገቡ የመወሰን፣
- ልጅ ወይም ልጆች መውለድ ይኑርባቸው አይኑርባቸው፣ መቼ እና በምን መንገድ፣ እንዲሁም ስንት ልጆች እንደሚወልዱም የመወሰን፣
- ከላይ የተጠቀሱትን ለማሳካት አስፈላጊ የሆኑትን መረጃዎች፣ ሀብቶች፣ አገልግሎቶች እና ድጋፍ ከመድልዎ፣ ከግዳጅ፣ ከብዝበዛ እና ከጥቃት ነፃ ሆነው የማግኘት ሰብአዊ መብቶች ላይ ነው።

**የጉትማከር -ላንሴት ኮሚሽን ከወሲባዊና የስነተዋልዶ ጤና እና መብቶች የተሟላ ብያኔ ጋር የሚስማማ የመሠረታዊ የወሲባዊና የስነተዋልዶ ጤና ሥራዎች ጥቅልም በምክረ ሐሳብነት ያቀርባል።** የወሊድ መቆጣጠሪያ አገልግሎቶችን፣ የእናቶች እና ጨቅላ ሕፃናት ክብካቤ እና ኤችአይቪ ኤድስን መከላከል እና ሕክምናንም ጨምሮ፣ ጥቅሉ የታወቁትን የወሲባዊና የስነተዋልዶ ጤና ጉዳዮችን ያካትታል። እንዲሁም ጥቅሉ የወሲባዊና የስነተዋልዶ ጤና እና መብቶችን በምልዓት ለመድረስ አስፈላጊ የሆኑትን እጅግም ያልተሠራባቸውንም አገልግሎቶች ያካትታል፡- ከኤችአይቪ ውጭ ላሉ የአባላዘር በሽታዎች ክብካቤ፤ አጠቃላይ የነገረ ወሲብ ትምህርት፤ ደህንነቱ የተጠበቀ የፅንስ ማቋረጥ ክብካቤ፤ በጾታ ላይ የተመሠረተ ጥቃት መከላከል፣ መለየት እና ማማከር፤ መሃንነትን እና የማህጸን ጫፍ ካንሰርን መከላከል፣ መለየት እና ማከም፤ እንዲሁም የወሲባዊ ጤና እና ደህንነት ምክር እና ክብካቤ።

ኮሚሽኑ ሃገራት የዚህን የአገልግሎቶች ጥቅል ተደራሽነት፣ የሀብት እና የፖሊሲ ሁኔታዎች በፈቀዱት መጠን፣ በሂደት እንዲያስፋፉ፣ ሁልጊዜም ተጋላጭ ለሆኑት እና ለተገለሉ የሕብረተሰብ ክፍሎች ፍላጎት ቅድሚያ እንዲሰጡ ምክረ ሐሳቡን ያቀርባል። ከአዲሱ ብያኔ ጋር የሚስማሙት መሠረታዊ የወሲባዊ እና የስነተዋልዶ ጤና አገልግሎቶች የህክምና ስነምግባር፣ የሕብረተሰብ ጤና እና ሰብዓዊ መብቶች፡- የጤና መብትን "የተገኘነት፣ የተደራሽነት፣ የተቀባይነት እና የጥራት" ማዕቀፍን ጨምሮ ዓለማቀፍ የጥራት ደረጃዎችን ማሟላት አለባቸው።

### መሠረታዊ የወሲባዊ እና የስነተዋልዶ ጤና ሥራዎች ጥቅል

- ➔ አጠቃላይ የነገረ ወሲብ ትምህርት
- ➔ ዝቅተኛ መጠናቸው እና ዓይነቶቻቸው ለተወሰኑ የተለያዩ ዘመናዊ የወሊድ መቆጣጠሪያዎች ምክር እና አገልግሎቶች
- ➔ ቅድመ ወሊድ፣ ወሊድ እና ድህረ ወሊድ ክብካቤ፤ ድንገተኛ ማዋለድን እና የጨቅላ ሕፃናት ክብካቤን ጨምሮ
- ➔ ደህንነቱ የተጠበቀ የጽንስ ማቋረጥ አገልግሎት እና ደህንነቱ ባልተጠበቀ የጽንስ ማቋረጥ ምክንያት ለሚያጋጥሙ የጤና ችግሮች የሚሰጥ ህክምና
- ➔ ኤችአይቪን እና ሌሎች በወሲባዊ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎችን መከላከል እና ማከም
- ➔ ወሲባዊ እና የጾታ ጥቃትን መከላከል፣ መለየት፣ ፈጣን አገልግሎቶች መስጠት እና ወደተገቢው ህክምና መላክ
- ➔ የስነተዋልዶ ካንሰሮችን፣ በተለይም የማህጸን ጫፍ ካንሰርን መከላከል፣ መለየት እና መቆጣጠር
- ➔ የከፊል መሀንነት እና የመሀንነት መረጃ፣ ምክር እና አገልግሎቶች
- ➔ የስነተዋልዶ ጤና እና ደህንነት ምክር እና አገልግሎቶች መረጃ

# የወሲባዊና የስነተዋልዶ ጤና አገልግሎቶችን የመስጠት ወጪዎች እና ጥቅሞች

**ለእነዚህ አገልግሎቶች ያሉትን ፍላጎቶች በሙሉ መድረስ ለአብዛኞቹ ሀገራት የሚቻል ነው።** ለምሳሌ፣ በማደግ ላይ ባሉ ክፍለ ዓለማት፣ የሴቶችን የዘመናዊ ወሊድ መቆጣጠሪያ ፍላጎቶች ሙሉ በሙሉ ለማሟላት እና በዓለም የጤና ድርጅት ምክረ ሐሳብ መሠረት ለሁሉም ነፍሰ ጡር ሴቶች (የጽንስ መጨንገፍን፣ የሙት ወሊዶችን፣ ጽንስ ማቋረጥን እና የሕያው ወሊዶችን ጨምሮ) እና ለጨቅላ ሕፃናት የጤና አገልግሎቶችን ለማቅረብ የሚያስፈልገውን ጠቅላላ ወጪ በዓመት በግምት በ9 የአሜሪካ ዶላር በነፍስ ወከፍ መሸፈን ይቻላል።

ኢንቨስትመንቶቹም ትልቅ ትርፍ ያስገኛሉ። ማስረጃዎች እንደሚያሳዩት፣ የወሲባዊና የስነተዋልዶ ጤና አገልግሎቶች ተደራሽነት ህይወቶችን ያድናል፣ ጤናን እና ደህንነትን ያሻሽላል፣ የጾታ እኩልነትን ያበረታታል፣ ምርታማነትን እና የቤተሰብ ገቢን ይጨምራል፣ እንዲሁም የልጆችን ጤና እና ደህንነት በማሻሻልም ለብዙ ትውልዶች የሚተርፍ ጥቅም ያስገኛል። እጅግ በጣም የቅርቦቹ መረጃዎች እንደሚያሳዩት፣ በታዳጊ ክፍለ ዓለማት የዘመናዊ የወሊድ መቆጣጠሪያ ፍላጎቶችን ሙሉ በሙሉ ማሟላት እና ነፍሰጡር ሴቶች እና ጨቅላ ሕፃናቶቻቸው መሠረታዊውን ክብካቤ እንዲያገኙ ማድረግ፣ ከ2017 ጀምሮ ቀጥሎ ያሉት የመቀነስ ውጤቶች አስገኝቷል፡ - በ67 ሚሊዮን ያነሱ ያልታቀዱ እርግዝናዎች (የ75% ቅነሳ) በ2.2 ሚሊዮን ያነሱ የጨቅላ ሕፃናት ሞቶች (የ80% ቅነሳ) እና በ224,000 ያነሱ የእናቶች ሞቶች (የ73% ቅነሳ)። እነዚህ ጥቅሞች በብዙ ዓመታት ውስጥ የትርፍ ክፍያዎችንም ከማስገኘታቸው በተጨማሪ፣ የሌሎች የልማት ግቦችን ስኬትም ያሳልጣሉ።

# የወሲባዊና ስነተዋልዶ ጤና እና መብቶችን መረጃዎችና አገልግሎቶችን ሁለንታዊ ተደራሽነት የሚያሳካ ፍኖተ ካርታ

**በመጨረሻ፣ ኮሚሽኑ ከፍተኛ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ተግባራት** በብሔራዊ፣ ክፍለ ዓለማዊ እና ዓለማቀፋዊ የፖሊሲ አውጪዎች፣ አስተማሪዎች፣ እና የጤናና የመብቶች ተሟጋቾች እንዲከወኑ ምክረ ሐሳብ ያቀርባል። እነዚህ ምክረ ሐሳቦች በማስረጃ ላይ የተመሠረቱ እና ሰብዓዊ መብቶችንም መነሻዎቻቸው ያደረጉ፤ እንዲሁም በጤና አገልግሎቶች ላይ ያሉ ክፍተቶችን እና ሰዎች የወሲባዊና ስነተዋልዶ ጤና እና መብቶችን ሙሉ በሙሉ እንዳያሳኩ የሚያግዱ ማኅበራዊ፣ ባህላዊ እና ኢኮኖሚያዊ መሰናክሎችንም - ጾታ ላይ ያነጣጠሩትን ጨምሮ- የሚዳስሱ ናቸው።

- የሪፖርቱን የተሟላ የወሲባዊና ስነተዋልዶ ጤና እና መብቶች ብያኔ ተቀብሎ ተግባራዊ ማድረግ፤ ለወሲባዊ እና ስነተዋልዶ መብቶች ልዩ ትኩረት መስጠት
- ሰዎች ሁሉ የወሲባዊና ስነተዋልዶ ጤና እና መብቶቻቸውን እንዲገነዘቡ፣ እንዲጠብቁ እና እንዲያሳኩ እንዲሁም የሌሎችንም መብቶች እንዲያከብሩ የሚያስችሉ የህጎች፣ የፖሊሲዎች እና የማህበራዊ ደንቦች እና መዋቅሮችን ለውጦች መደገፍ
- የመሠረታዊውን፣ የተቀናጀ የወሲባዊና የስነተዋልዶ ጤና ሥራዎች ተደራሽነት ቀስ በቀስ ማስፋፋት፣ ወዲያውም የችግር ተጋላጭ እና የተገላይ ሕዝቦች ፍላጎቶች መደረሳቸውን ማረጋገጥ
- መሠረታዊውን ወሲባዊ እና የስነተዋልዶ ጤናን የተሟላ ተደራሽነት ለማሳካት የሚያችል ዘላቂ የአገር ውስጥ እና ዓለማቀፍ የገንዘብ ድጋፍን አስተማማኝነት ማረጋገጥ
- በፕሮግራም አተገባበር ላይ በተደጋጋሚ ችላ በሚባሉ፣ ሆኖም በብዙ ሰዎች ላይ ተፅዕኖ ባላቸው የወሲባዊና የስነተዋልዶ ጤና እና መብቶች ጉዳዮች ላይ እርምጃ መውሰድ፤ እነዚህ ጉዳዮች የሚከተሉትን ያካትታሉ:-
  - ደህንነታቸው የተጠበቀ የጽንስ ማቋረጥ አገልግሎቶችን ማቅረብ እና አስፈላጊ በሚሆንበት ቦታ የጽንስ ማቋረጥ ህጎችን ማላላት
  - ወጣቶች የወሲባዊ እና የስነተዋልዶ ጤና መረጃዎችን እና አገልግሎቶችን ያለ አድልዎ ማግኘታቸውን ማረጋገጥ
  - ወሲባዊ እና ጾታን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶችን በፖሊሲዎች፣ በአገልግሎቶች እና በመከላከል ፕሮግራሞች አማካይነት መድረስ
  - ወንዶች የሴቶችን ጤና፣ መብቶች እና ነፃነት እንዲደግፉ ማሳተፍ እና የወንዶችን የወሲባዊና የስነተዋልዶ ጤና እና መብቶች ፍላጎቶችም መድረስ
- በተደጋጋሚ ጊዜ ለሚገለሉ፣ ለሚጎዱ እና ለመድልዎ ለሚጋለጡ ቡድኖች ተጨማሪ ድጋፍ መስጠት:-
  - የተፈናቃዮችን እና የስደተኞችን የወሲባዊና የስነተዋልዶ ጤና እና መብቶች መጠበቅ እና በሰብአዊ ድጋፍ መስጫ አውዶች ያሉ አገልግሎቶችን ማጠናከር
  - የተለያዩ ወሲባዊ ሁኔታዎች፣ ጾታዊ ማንነቶች እና መግለጫዎች እና ወሲባዊ ባህርያት ላሏቸው ሰዎች የወሲባዊ እና የስነተዋልዶ ጤና እና መብቶች እውቅና መስጠት እና መድረስ
- ለማስረጃዎች ክፍተቶች ትኩረት መስጠት እና የፖሊሲ እና ፕሮግራም ውሳኔ ለመስጠት ለሚያስፈልግ የወሲባዊና የስነተዋልዶ ጤና እና መብቶች ምርምር ቅድሚያ መስጠት
- የወሲባዊና የስነተዋልዶ ጤና እና መብቶች ግቦች እና ቃል የተገባባቸው ጉዳዮች እውን መሆናቸውን ለማረጋገጥ በሁሉም ደረጃዎች የተጠያቂነት ሂደትን ማጠናከር እና መጠቀም

# ዕድገትን ማፋጠን

**ሁሉም ሰዎች ምስጢራቸው የተጠበቀ፣ በአክብሮት የሚሰጡ እና ከፍተኛ ጥራት ያላቸው የወሲባዊና የስነተዋልዶ ጤና አገልግሎቶች ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ የሚያስፈልጉን ዕውቀቶች እና መሳሪያዎች -** በዓለማቀፋዊ መመሪያዎች፣ በፕሮቶኮሎች፣ በቴክኖሎጂ እና በምርጥ ተመክሮዎች ማስረጃዎች መልክ - አሉን። በርካታ ስኬታማ ሥራዎችም ዝቅተኛ እና መካከለኛ ገቢ ባላቸው ሀገራት ተሞክረዋል። እንዲያም ሆኖ፣ ብዙ ጊዜ፣ እነዚህ አመርቂ ዘዴዎች በስፋት ሥራ ላይ አይውሉም፣ የአጠቃላዩ የወሲባዊና የስነተዋልዶ ጤና እና መብቶች ማስፈጸሚያ ዘዴ ሆነው አይቀናጁም፣ ወይም ለተጋላጭ ወይም ለተገለሉ ቡድኖች ለመድረስም አይችሉም።

ዕድገቱን ለማፋጠን፣ መንግሥታት እና ዕርዳታ ሰጪዎች ሰዎችን ሁሉ የሚጠቅመውን የወሲባዊና ስነተዋልዶ ጤና እና መብቶች ሠፊ እና የላቀ አጀንዳ የግድ መቀበል አለባቸው። የሲቪል ማኅበራት ቡድኖች እና ሌሎች የወሲባዊና ስነተዋልዶ ጤና እና መብቶችን የማላቅን መሠረታዊ ጠቀሜታዎች የተገነዘቡ ሁሉ በየዘርፉ ሊተጉ እና መንግሥታትንም ለኃላፊነቶቻቸው ተጠያቂ ሊያደርጓቸው ይገባል። በማስረጃ ላይ ለተመሠረተ - ጤናን ለሚያሻሽል እና ሰብአዊ መብቶችንም ለሚያስከብር - የወሲባዊና ስነተዋልዶ ጤና እና መብቶች ፖሊሲ እና መርሐ ግብር የሚወሰድ የጋራ ኃላፊነት፣ የግለሰቦችን ሁሉ ያለስጋት፣ የተሳካ ህይወት የመኖር እና ዓለማቀፍ የልማት ግቦችን የማሳካት አቅም ለመደገፍ ወሳኝነት አለው።

## ምስጋና

ሙሉ ሪፖርቱ በሜይ 2018 ዘ ላንሴት ላይ ታትሟል፤ ይኸውም እውን የሆነውም ለጉትማከር ኢንስቲቲዩት ከደች የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ከዩኬ መንግሥት የዩኬ ኤይድ፣ ከኖርዌይ የልማት ትብብር ድርጅት፣ ከጀርመን ፌዴራል የኢኮኖሚ ትብብር እና ልማት ሚኒስቴር፣ እና ከዴቪድ እና ሉሲል ፓካርድ ፋውንዴሽን በተገኘ ድጋፍ ነው። በሪፖርቱ ውስጥ ያሉት ግኝቶች እና ድምዳሜዎች የጸሐፊዎቹን እንጂ የዕርዳታ ሠጪዎቹን አቋሞች እና ፖሊሲዎች የግድ አያሳዩም።

**ሙሉ ሪፖርቱ የዘ ላንሴት ድረገጽ ላይ ይገኛል፡-**
**www.thelancet.com/commissions/sexual-and-reproductive-health-and-rights**

# ጉትማከር - ላንሴት

## ኮሚሽን

ስለወሲባዊና ስነተዋልዶ
ጤና እና መብቶች

www.thelancet.com/commissions/
sexual-and-reproductive-health-and-rights